የመሪዎች ቃል ኪዳን

እና

የጥናት መመሪያ

ወደ መሪዎች ቃል ኪዳን እንኳን ደህና መጡ።

ይህ ቃል ኪዳን በመጀመሪያ የተዘጋጀው በሉዛን የመሪዎች ዲቨሎፕመንት ኮሚቴ ግባት እንዲሆን ታስቦ በሉዛን ኬፕታውን በ 2010 በተካሄደው ዓለም አቀፍ የወንጌል ስርጭት ኮንፍራንስ የቀረበ ነው።

MentorLink INTERNATIONAL

ተጨማሪ የሜንቶር ሊንክ ምንጮችን ለማግኘት ይህንን ገጽ ይመልከቱ:

www.MentorLink.org

በእርሱ መንግስት ውስጥ ኢየሱስ እና ሐዋርያት ብዙ የሚያስተምሩን ነገር አለ፡-

>በሰሩት ሥራ
>ከሰዎች ጋር በነበራቸው ግኑኝነት
>ስለራሳቸው በነበራቸው አመለካከት
>ትክክለኛ ተነሳሽነት ምን እንደሚመስል
>በንግግራቸውም ሆነ በድርጊታቸው በሚያስተላልፉት መልዕክት

ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ ኢየሱስ እና ሐዋርያት ሰለ ሐሰተኛ መሪዎች አስጠንቅቀዋል።
በአብዛኛው የአዲስ ኪዳን ደብዳቤዎች ሐሰተኛ መሪዎች በሚገባ ተብራርተዋል። ስለዚህም
ይኸ ነገር በቀላሉ መታየት የለበትም።

የመሪዎች ኪዳን የተዘጋጀው በዓለም ሁሉ ለሚገኙ መሪዎች ስለነዚህ እውነቶች በቀላሉ ለመዘርዘር ነው።እኛ ይህንን ቃልኪዳን እርሶ እንዲያነቡና ምስክር ባለበት እንዲፈርሙ እናበረታታዎታለን። ከዛም ለሌላ እንዲያስተላልፉም እንጠይቆታለን።

ለዚህ እርሶ የሚያወጡት ምንም ወጪ የለም። የእኛ ሽክምና ራዕይ በመንግስቱ ውስጥ ያሉ
መሪዎች በብቃት እንዲመሩና ክርስቶስን የሚመስሉ ሌሎች መሪዎችን እንዲያነሳብቱ ለማስቻል ነው።

የተሰጡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማንበብና የአምልኮ ጊዜ መውሰድ ጠቃሚ መሆኑን ሊገነዘቡ እንደሚችሉ እናስባለን። እኛ ይህንን ለሌሎች እንዲያከፋፍሉ እናበረታታወታለን።
ምንም መሻሻል ሳይደረግበት ይህንን ለሌሎች ማስተላለፍ ተፈቅዶአል። የመሪዎች ቃልኪዳን የተገነባው በ1974 በሎዛን ቃልኪዳን (Lausanne Covenant) መሰረት ላይ ነው። ይህ ቃል ኪዳን በመጀመሪያ የተዘጋጀው በሎዛን የመሪዎች ዲቨሎፕመንት **ኮሚቴ** ግባት እንዲሆን ታስቦ በሎዛን (Lausanne) ኬፕታውን በ 2010 ለተካሄደው ለዓለም አቀፍ የወንጌል ስርጭት ኮንፍራንስ ነው።

መግቢያ

እንደመሪ በመንጋው መካከል ኢየሱስ ክርስቶስን እንዳገለግል የጠራኝን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። እርሱ በዚህ ምድር እንደተመላለሰ እና ሰዎችን እንዳሳደገ እኔም እርሱን በመምሰል በሙሉ ልቤ ጌታዬን እና መሪዬን ኢየሱስን መከተል እፈልጋለሁ። እንደመሪ ክርስቶስን በመምሰል ለማደግና በሌሎችም ላይ አሉታዊ ተጽህኖ ለማሳደር ተስማምቼያለሁ። በእርሱ ጸጋ ክርስቶስን ለመመሰልና እንደርሱ ለመምራት እራሴን አዘጋጃለው።

(ማሳሰቢያ በዚህ ቃልኪዳን መሪ ስንል መጋቢ፤ ሐዋሪያ፤ የቤተክርስትያን ሽማግሌ፤ ጳጳስ ፤ ዲያቆን ፤ ወንጌላዊ፤ አስተማሪ፤ ሚሶናዊ፤ ነቢይ፤ የግብይት ቦታ መሪ፤ የትናንሽ ቡድን መሪ ፤ አስተማሪ፤ የቤት አምልኮ መሪ፤ እንዲሁም እንደክርስቶስ መምራት የሚፈልግ ማንም ሰው ሊሆን ይችላል። ይህም ወንድ፤ ሴት፤ ወጣት፤ ሽማግሌ፤ የሞያ ሚኒስትሪ ሰራተኞችን፤ ምህመንን ያጠቃልላል።)

የመሪዎች ቃል ኪዳን የጥናት መመሪያ

ይህንን መሳሪያ እንዴት ነው የምንጠቀመው:
ለዚህ ሂደት የማያቋርጥ ጸሎት ቁልፍ ስለሆነ ማድረጎን ያረጋግጡ። የሕይወት ለውጥን ማምጣት የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ በእርሱ መደገፍ አለብን። የመሪዋች ቃልኪዳንን የሚጠቀም ሰው ሲያገኙም ሆነ ከትናንሽ ቡድን በጋራ ሲያጠኑ ከዚህ በታች በተዘረዘሩ አስር ዓረፍተ ነገሮች ጎን ለጎን በተሰጡ አራት ጥያቄዎች ላይ ትኩረት ያድርጉ። ተዋረድን የጠበቀ፤ የተማሩትን ወደተግባር የሚቀይሩበትን ድርጊት ያካተተ፤የሚፈጸምበትን ጊዜ ታሳቢ ያረገ እና አጠቃላይ ሂደቱን ለመከታተል የሚረዳዎትን ሰነድ ያዘጋጁ።

©MentorLink 2022.

የመሪዎች ቃል ኪዳን እና የጥናት መመሪያ

(Leaders Covenant Reflection Questions)

1. እኔ ለኢየሱስ ተጠያቂ ሆኛለሁ።

እኔ ጌታዬ ለሆነው ክርስቶስ ተጠያቂ ነኝ፡፡ እርሱ ይገመግመኛል፣ ይሸልመኛልም፡፡ እኔ ለጌታዬ፣ ለመንግሥቱና ለእርሱ ሕዝብ ደስታና ራሴን ሰውቼ ለማገልገል ዝንተ ሕይወቴን ሁሉ ለማገልገል ተጠርቼአለሁ፡፡ ለእርሱና ለሕዝቡ አገልግሎት ሲሉ ራሳቸውን ሰውተው የሚያገለግሉትን ስመለከት እጽናናለሁ፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ሌሎችን እንዴት እንደሚያሰተናግዱ፣ አገልግሎታቸውን እንዴት እንደሚያገለግሉና ሰዎችን እንዴት እንደሚመሩ ክርስቶስን እንደ ግድየለሽ አድርገው የሚመለከተቱትን ሳይ በጣም አዝናለሁ፡፡ እነርሱ በአደባባይ ሊመሰገኑ በመፈለግ እና በማሰብ ጊዜያዊ የሆነ ታይታን በማግኘት እንደሚሰሩ አውቃለሁ፡፡ ይሁን እንጂ በስውር የሚሆነውን ሁሉ በምሥጥር(በስውር) የሚመለከተው አባቴ ማንም ሳያያቸው ቀና ተግባርን የሚከውኑትን ያከብራቸዋል፤ይሸልማቸዋል፡፡ ስለዚህ ድፍረትን ለማግኘት፣ ብርታትንና እምነትን አግኝቼ ጌታዬን ለማስደሰትና በትክክለኛው መንገድ ለመምራት በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

(ማቴ. 6፡1-6፣ ማቴ. 16፡24-27፣ ሉቃ. 18፡28-30፣ ዮሐ. 5፡22-23፣ 1ኛቆሮ. 3፡10-15፣ 1ኛቆሮ. 4፡5፣ 2ኛቆሮ. 4፡11-18፣ 2ኛቆሮ. 5፡9-10፣ 2ኛቆሮ. 10፡12-18፣ 2ኛጢሞ. 4፡1-8)

1. እኔ አሁን በደረስኩበት የክርስትና ህይወትና አገልግሎት፡- ይኸ አንቀጽ ከሚያስተላልፈው መልህክት ውስጥ ለእኔ ጎላ ያለ ጠቀሜታ ያለው ነጥብ ምንድን ነው? (አንቀጹ ያዘለውን መልህክት ይዘህ(ይዘሽ) ለመቅረብ ሞክር(ሞክሪ)፡- አትቸኩል (አትቸኩዪ)።

_____

_____

_____

_____

2. በዚህ ጥናት መሠረት እራሴን ሳየው፡- ቀና የሆነ አስተዳደጌን ህይወቴ የሚያንጸባርቀው በምን መልኩ ነው? (አጽንዖት ስጥ(ስጪ) = የምታበረታታ ሁን(ሁኚ)

_____

_____

_____

_____

3. በዚህ አንቀጽ ከተንጸባረቀው መሰጠት ውስጥ አንድ ፤ሁለት ብዬ የምዘረዝረው የእኔ ደካማ ጎን ምንድን ነው? (ልታሻሽለው(ልታሻሽይው) ወይም ልታሳደገው(ልታሳድጊው) በሚገባህ(በሚገባሽ) ነገር ላይ ብቻ ትኩረትህን(ትኩረትሽን) አድርግ (አድርጊ)።

_____

_____

_____

_____

4. መሻሻልን በህይወትህ እና በአገልግሎትኸ ለማምጣት እኛ አብረን እየሰራን ሳለ፤አንተ ያንተን መሰጠት ሙሉ ለማድረግ (ለእያንዳንዱ ግብ) የምትወስዳቸው አንድ ፤ሁለት ብለኸ የምትገልጻቸው መሰረታዊ ተግባራዊ እርምጃዎች ምንድን ናቸው? (መሻሻልን የሚገዳደሩ ተግዳሮቶችን ለማስወገድ፡- በቅደም ተከተል መከተል የሚገባህን (የሚገባሽን) አስተማሪ (መካሪ) ነጥቦችን ጻፍ (ጻፊ)።

_____

_____ጊዜው_____

_____

_____ጊዜው _____

2. እኔ እንደ ኢየሱስ ዓይነት ሕይወት እኖራለሁ።

ክርስቶስን መሰል ባህሪ ለመሪነት አገልግሎት የግድ ነው፡፡ በኢየሱስ አቅጣጫ በመጓዝም ይገኛል፡፡ እኔ በኢየሱስ የምድር ላይ ቆይታ ጊዜዬ ለመሪነት ሚናቸው ውጫዊ ምልክቶች ልዩ ትኩረት ይሰጡ ለነበሩት ነገር ግን ልባቸው እና ባህሪያቸው ከአብ የራቀ እንደነበሩት ፈሪሳውያን ከመሆን ራሴን ለመጠበቅ እሻለሁ፡፡ በዚህ ዘመን ጾታዊ ፈተናዎች እጅግ የበዙ እንደሆኑ አውቃለሁ፡፡ ሆኖም ጌታችን በሃሳብም ሆነ በሥራ የቅድስና እና እግዚአብሔርን የመምሰል ሕይወት እንዲኖረን እንደጠራን እረዳለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜ መሪዎች በታማኝነት እንደማይሠሩ ወይም ሊያገለግሉአቸው ለሚፈልጉት ሕዝብ እውነት እንደማይናገሩ ሳይ አዝናለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜ መሪዎች በጥላቻ እና በቅናት ተነሳስተው ክፍፍል ለመፍጠር በማሰብ የሌሎች መሪዎችን ስማቸውን ሲያጠፉ ወይም ሥራቸውን ሲያጥላሉ ስመለከት እከፋለሁ፡ ፡ እኔ በውስጣዊ ማንነቴም ሆነ በውጫዊ ማንነቴ የበለጠ ኢየሱስን ልመስል እና በልቤም ሆነ በሕይወቴ የእሱን ባህሪ ለማሳየት እጠማለሁ፡፡

(ማቴ. 23፡23-28፣ ዮሐ. 15፡1-5፣ ፊሊ. 1፡15-17፣ ፊሊ. 3፡15-17፣ ተሰ. 2፡1-12፣ 1ኛጢሞ. 3፡1-13፣ ቲቶ. 2፡11-15፣ 2ኛጴጥ. 3፡11-14፣ 1ኛዮሐ. 2፡6)

1. እኔ አሁን በደረስኩበት የክርስትና ህይወትና አገልግሎት፡- ይኸ አንቀጽ ከሚያስተላልፈው መልህክት ውስጥ ለእኔ ጎላ ያለ ጠቀሜታ ያለው ነጥብ ምንድን ነው? (አንቀጹ ያዘለውን መልህክት ይዘህ(ይዘሽ) ለመቅረብ ሞክር(ሞክሪ)፡- አትቸኩል (አትቸኩዪ)።

_____

_____

_____

_____

2. በዚህ ጥናት መሠረት እራሴን ሳየው፡- ቀና የሆነ አስተዳደጌን ህይወቴ የሚያንጸባርቀው በምን መልኩ ነው? (አጽንዖት ስጥ(ስጪ) = የምታበረታታ ሁን(ሁኚ)

_____

_____

_____

_____

3. በዚህ አንቀጽ ከተንጸባረቀው መሰጠት ውስጥ አንድ ፤ሁለት ብዬ የምዘረዝረው የእኔ ደካማ ጎን ምንድን ነው? (ልታሻሽለው(ልታሻሽይው) ወይም ልታሳደገው(ልታሳድጊው) በሚገባህ(በሚገባሽ) ነገር ላይ ብቻ ትኩረትህን(ትኩረትሽን) አድርግ (አድርጊ)።

_____

_____

_____

_____

4. መሻሻልን በህይወትህ እና በአገልግሎትኽ ለማምጣት እኛ አብረን እየሰራን ሳለ፤አንተ ያንተን መሰጠት ሙሉ ለማድረግ (ለእያንዳንዱ ግብ) የምትወስዳቸው አንድ ፤ሁለት ብለኽ የምትገልጻቸው መሰረታዊ ተግባራዊ እርምጃዎች ምንድን ናቸው? (መሻሻልን የሚገዳደሩ ተግዳሮቶችን ለማስወገድ፡- በቅደም ተከተል መከተል የሚገባህን (የሚገባሽን) አስተማሪ (መካሪ) ነጥቦችን ጻፍ (ጻፊ)።

_____

_____ጊዜው_____

_____

_____ጊዜው_____

3. ኢየሱስን አገለግላለሁ።

ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግስት በሕዝቡ ልብ እና ሕይወት ላይ ያለውን የእግዚአብሔርን መሪነት እና ገዢነት እየሰበከ መጣ፡፡ በአንጻሩ የሰዎች ተፈጥሮ ደግሞ መሪዎች የራሳቸውን ‹‹ግዛት›› ወይም ስርወ መንግስት እንዲመሠርቱ ይገፋፋቸዋል፡፡ አንዳንድ መሪዎች ከሕዝቡ ክብርን ሲፈልጉ እና ሙገሳን ሲሹ እና ከዚህም በላይ በኢየሱስ ላይ የነበረውን ትኩረት በራሳቸው ላይ እንዲሆን ሲያደርጉ ሳይ አዝናለሁ፡፡ እኔ ተልዕኮዬ የኢየሱስን መሪነት እና በሕዝቡ ልብ ውስጥ እንዲገዛ ማድረግ እንደሆነ አረጋግጣለሁ፡፡ እንዲሁም ኢየሱስን በማገልገል ሂደት ቤተሰቤን በመንፈሳዊ ባህሪ እንዳገለግል እና እንድመግብ እንደተጠራሁም አውቃለሁ፡፡ እኔ ኢየሱስን በሙሉ ልቤ ለማገልገል እሻለሁ፡፡

(ማቴ. 5፡1-12፣ የሐዋ. 28፡30-31፣ 2ኛቆሮ. 4፡1-2፣ ፊሊ. 2፡9-13፣ 1ኛጢሞ. 3፡1-5፣ 2ኛጴጥ. 2፡1-3፣ 3ኛዮሐ. 9–11)

1. እኔ አሁን በደረስኩበት የክርስትና ህይወትና አገልግሎት፡- ይኸ አንቀጽ ከሚያስተላልፈው መልህክት ውስጥ ለእኔ ጎላ ያለ ጠቀሜታ ያለው ነጥብ ምንድን ነው? (አንቀጹ ያዘለውን መልህክት ይዘህ(ይዘሽ) ለመቅረብ ሞክር(ሞክሪ)፡- አትቸኩል (አትቸኩዪ)።

_____

_____

_____

_____

2. በዚህ ጥናት መሠረት እራሴን ሳየው፡- ቀና የሆነ አስተዳደጌን ህይወቴ የሚያንጸባርቀው በምን መልኩ ነው? (አጽንዖት ስጥ(ስጪ) = የምታበረታታ ሁን(ሁኚ)

_____

_____

_____

_____

3. በዚህ አንቀጽ ከተንጸባረቀው መሰጠት ውስጥ አንድ ፤ሁለት ብዬ የምዘረዝረው የእኔ ደካማ ጎን ምንድን ነው? (ልታሻሽለው(ልታሻሽይው) ወይም ልታሳደገው(ልታሳድጊው) በሚገባህ(በሚገባሽ) ነገር ላይ ብቻ ትኩረትህን(ትኩረትሽን) አድርግ (አድርጊ)።

_____

_____

_____

_____

4. መሻሻልን በህይወትህ እና በአገልግሎትኽ ለማምጣት እኛ አብረን እየሰራን ሳለ፤አንተ ያንተን መሰጠት ሙሉ ለማድረግ (ለእያንዳንዱ ግብ) የምትወስዳቸው አንድ ፤ሁለት ብለኽ የምትገልጻቸው መሰረታዊ ተግባራዊ እርምጃዎች ምንድን ናቸው? (መሻሻልን የሚገዳደሩ ተግዳሮቶችን ለማስወገድ፡- በቅደም ተከተል መከተል የሚገባህን (የሚገባሽን) አስተማሪ (መካሪ) ነጥቦችን ጻፍ (ጻፊ)።

_____

_____ጊዜው_____

_____

_____ጊዜው_____

4. እንደ ኢየሱስ ባለ መንገድ እመራለሁ።

ጌታችን ወደ ምድር በመጣ ጊዜ በእርሱ መንግስት ውስጥ መሪዎች እንዲሆኑ እና እንዲያደርጉ የሚፈልገውን ምሳሌ ሆኖ አሳይቷል አስተምሯልም፡፡ እርሱ እኛ የግድ በትህትና እና በቅንነት መመላለስ እንዳለብን መስቀላችንን ዕለት ዕለት ተሸክመን ሰዎችን በጸጋ እና በአክብሮት መያዝ እንዳለብን አስተምሮናል፡፡ እርሱ ሥልጣኑን በማንም ላይ በግድ አልተጠቀመም፡፡ ኢየሱስ የራሱን የማዕረግ ሥልጣን የሚመራቸውን አቅጣጫ ፣ለማስያዝ ለመባረክ እና ለመጥቀም ነበር የተጠቀመበት፡፡ እኛም በተመሳሳይ መንገድ እንድንመራ ጠርቶናል፡፡ ብዙ መሪዎች ያላቸውን የማዕረግ ሥልጣን በሰዎች ላይ «ጌታ» ለመሆን እና ይልቁንም የዓለምን የኃይል አመራር ልምምድ እና እሴቶች ይጠቀማሉ፡፡ እኔ አንዳንድ መሪዎች ምንም እንኳን ትክክለኛውን አስተምህሮ ቢናገሩም የክርስቶስን መሰል መሪ ሕይወት ስለማይኖሩ አዝናለሁ፡፡ የእነርሱ ተግባራት የክርስቶስን የአመራር ትምህርቶች ያዘበራርቃሉ፡፡ በዚህም ሊያገለግሉአቸው የተጠሩትን ሕዝብ ግራ ያጋባሉ፡፡ እኔ በትህትና እንደ ኢየሱስ ሆኖ የሚያገለግል ልብ እንዲኖረኝ እጠይቃለሁ/ ጸልያለሁ፡፡

(ማቴ. 18፡1-4፣ ማቴ. 23፡1-12፣ ማር. 10፡42-45፣ 2ኛቆሮ. 11፡12- 21፣ 2ኛጢሞ. 3፡1-13፣ ዕብ. 1፡1-2፣ 1ኛጴጥ. 5፡1-5)

1. እኔ አሁን በደረስኩበት የክርስትና ህይወትና አገልግሎት፡- ይኸ አንቀጽ ከሚያስተላልፈው መልህክት ውስጥ ለእኔ ጎላ ያለ ጠቀሜታ ያለው ነጥብ ምንድን ነው? (አንቀጹ ያዘለውን መልህክት ይዘህ(ይዘሽ) ለመቅረብ ሞክር(ሞክሪ)፡- አትቸኩል (አትቸኩዪ)።

_____

_____

_____

_____

2. በዚህ ጥናት መሠረት እራሴን ሳየው፡- ቀና የሆነ አስተዳደጌን ህይወቴ የሚያንጸባርቀው በምን መልኩ ነው? (አጽንዖት ስጥ(ስጪ) = የምታበረታታ ሁን(ሁኚ)

_____

_____

_____

_____

3. በዚህ አንቀጽ ከተንጸባረቀው መሰጠት ውስጥ አንድ ፤ሁለት ብዬ የምዘረዝረው የእኔ ደካማ ጎን ምንድን ነው? (ልታሻሽለው(ልታሻሽይው) ወይም ልታሳደገው(ልታሳድጊው) በሚገባህ(በሚገባሽ) ነገር ላይ ብቻ ትኩረትህን(ትኩረትሽን) አድርግ (አድርጊ)።

_____

_____

_____

_____

4. መሻሻልን በህይወትህ እና በአገልግሎትኽ ለማምጣት እኛ አብረን እየሰራን ሳለ፤አንተ ያንተን መሰጠት ሙሉ ለማድረግ (ለእያንዳንዱ ግብ) የምትወስዳቸው አንድ ፤ሁለት ብለኽ የምትገልጻቸው መሰረታዊ ተግባራዊ እርምጃዎች ምንድን ናቸው? (መሻሻልን የሚገዳደሩ ተግዳሮቶችን ለማስወገድ፡- በቅደም ተከተል መከተል የሚገባህን (የሚገባሽን) አስተማሪ (መካሪ) ነጥቦችን ጻፍ (ጻፊ)።

_____

_____ጊዜው_____

_____

_____ጊዜው_____

5. መሪዎችን አሳድጋለሁ።

በኢየሱስ ዋና ትኩረት ከተሰጣቸው ሥራዎች አንዱ መሪዎችን ማፍራት ነበር፡፡ እርሱ ብዙ መሪዎችን አላመረተም ነገር ግን ሆነ ብሎ ጥቂት ቁጥር በነበራቸው ላይ ብቻ ነበር ትኩረቱን ያደረገው፡፡ ኢየሱስ እንዳደረገው እኔ መሪዎችን ማፍራት ተስፋ ካላቸው ወንዶች እና ሴቶች ጋር የቅርብ እና የግል ግንኙነቶች እንድፈጥር እና እነርሱን ለማብቃት (ብቁ ለማድረግ) ጊዜዬን መስዋዕት እንዳደርግ ጥሪ እንደሚያደርግልኝ አረጋግጣለሁ፡፡ እኔ በዓለም ዙሪያ ያሉ የበርካታ ወጣት መሪዎች የልብ ጩኸት መንፈሳዊ ምሳሌነት ያለው አለማማጅ ስለማግኘት መሆኑን እረዳለሁ፡፡ እንዲሁም እኔ ቅዱሳንን ለአገልግሎት የማስታጠቅ እና መንፈስ ቅዱስ በሚያመለክታቸው አቅጣጫ እንዲያገለግሉ የመልቀቅ ጥሪ እውቅና እሰጣለሁ፡፡ እናም ደግሞ በርካታ መሪዎች ይህንን ነገር ማስቀደምን ችላ እንዳሉም አውቃለሁ፡፡ እኔ በአትኩሮት ቅዱሳንን ለማስታጠቅ እና የወጣት መሪዎችን ልብ እና ሕይወት ለማጠናከር እንድችል ጸጋ እና እይታ እንዲሰጠኝ እጸልያለሁ/ እጠይቃለሁ፡፡

(ማቴ. 4፡18-22፣ ማቴ. 28፡16-20፣ ሉቃ. 6፡12-16፣ ዮሐ. 17፡6- 19፣ ሐዋ. 11፡22-26፣ ሐዋ. 15፡9-16፡5፣ ፊሊ. 2፡19-30፣ 2ጢሞ.)

1. እኔ አሁን በደረስኩበት የክርስትና ህይወትና አገልግሎት፡- ይኸ አንቀጽ ከሚያስተላልፈው መልህክት ውስጥ ለእኔ ጎላ ያለ ጠቀሜታ ያለው ነጥብ ምንድን ነው? (አንቀጹ ያዘለውን መልህክት ይዘህ(ይዘሽ) ለመቅረብ ሞክር(ሞክሪ)፡- አትቸኩል (አትቸኩዪ)።

_____

_____

_____

_____

2. በዚህ ጥናት መሠረት እራሴን ሳየው፡- ቀና የሆነ አስተዳደጌን ህይወቴ የሚያንጸባርቀው በምን መልኩ ነው? (አጽንዖት ስጥ(ስጪ) = የምታበረታታ ሁን(ሁኚ)

_____

_____

_____

_____

3. በዚህ አንቀጽ ከተንጸባረቀው መሰጠት ውስጥ አንድ ፤ሁለት ብዬ የምዘረዝረው የእኔ ደካማ ጎን ምንድን ነው? (ልታሻሽለው(ልታሻሽይው) ወይም ልታሳደገው(ልታሳድጊው) በሚገባህ(በሚገባሽ) ነገር ላይ ብቻ ትኩረትህን(ትኩረትሽን) አድርግ (አድርጊ)።

_____

_____

_____

_____

4. መሻሻልን በህይወትህ እና በአገልግሎትኽ ለማምጣት እኛ አብረን እየሰራን ሳለ፤አንተ ያንተን መሰጠት ሙሉ ለማድረግ (ለእያንዳንዱ ግብ) የምትወስዳቸው አንድ ፤ሁለት ብለኽ የምትገልጻቸው መሰረታዊ ተግባራዊ እርምጃዎች ምንድን ናቸው? (መሻሻልን የሚገዳደሩ ተግዳሮቶችን ለማስወገድ፡- በቅደም ተከተል መከተል የሚገባህን (የሚገባሽን) አስተማሪ (መካሪ) ነጥቦችን ጻፍ (ጻፊ)።

_____

_____ጊዜው_____

_____

_____ጊዜው_____

6. ፊቱን እፈልጋለሁ።

ጌታችን በትህትና እና በእርሱ በመደገፍ የሚጓዙትን እና ፊቱን በኅብረት እና በጋራ ጸሎት የሚሹትን ያከብራል ከፍ ያደረጋል፡፡ ኢየሱስ በጸሎት ከእርሱ ጋር ኅብረት ለማድረግ እና የልቡን ፈቃድ ለማወቅ ከአባቱ ጋር ለብቻ ጊዜ የማሳለፍ መደበኛ ልምምድን አስተምሮናል፡፡ እርሱ ይህንን ያደርግ የነበረው ብዙ ፈላጊዎች በነበሩት እና ግፊቶች በነበሩበት ጊዜ እንዲሁም አስከፊ በሆኑ አጋጣሚዎች መካከል ሁሉ ሆኖ ነበር፡፡ የኢየሱስን ምሳሌ በመከተል እኔም በግል የኅብረት ጊዜ እና ጸሎት ጌታን ልገናኘው እፈልጋለሁ፡፡ ይኼ ደስ እንደሚያሰኘው እና እራሴንም ከእርሱ ጋር ከእርሱ መንገድ ጋር እና ከፈቃዱ ጋር ይበልጥ እንድቀራረብ እንደሚያደርገኝ አውቃሁ፡፡ እንዲሁም ሰዋዊ ውስንነቴን በመረዳት እረፍትን (የሰባተኛ ዓመት ሰንበት) በቋሚነት ጊዜ በመመደብ በመውሰድ ነፍሴን በማደስ ለመኖር እፈልጋለሁ፡፡ ይኼም ለተወሰነ ጊዜ ያህል ካለሁበት ዓለም ግፊቶች ተለይቼ ነፃ ሆኜ ቆይታ ማድረግ መሆኑንም አውቃለሁ፡፡ ልቤ እርሱ ወደ ቤቱ እስኪወስደኝ ድረስ ወይም በክብሩ እስኪመጣ ድረስ እድሜዬን በሙሉ በታማኝነት ማገልገል ላይ ነው ያለው፡፡

(ኢሳ. 66፡1-2፣ ማቴ. 14፡23፣ ማቴ. 26፡36-39፣ ማር. 1፡35-39፣ ሉቃ. 4፡42-43፣ ሉቃ. 5፡16፣ ፊሊ. 4፡5-7፣ 1ጴጥ. 5፡6-8)

1. እኔ አሁን በደረስኩበት የክርስትና ህይወትና አገልግሎት፡- ይኸ አንቀጽ ከሚያስተላልፈው መልህክት ውስጥ ለእኔ ጎላ ያለ ጠቀሜታ ያለው ነጥብ ምንድን ነው? (አንቀጹ ያዘለውን መልህክት ይዘህ(ይዘሽ) ለመቅረብ ሞክር(ሞክሪ)፡- አትቸኩል (አትቸኩዪ)።

_____

_____

_____

_____

2. በዚህ ጥናት መሠረት እራሴን ሳየው፡- ቀና የሆነ አስተዳደጌን ህይወቴ የሚያንጸባርቀው በምን መልኩ ነው? (አጽንዖት ስጥ(ስጪ) = የምታበረታታ ሁን(ሁኚ)

_____

_____

_____

_____

3. በዚህ አንቀጽ ከተንጸባረቀው መሰጠት ውስጥ አንድ ፤ሁለት ብዬ የምዘረዝረው የእኔ ደካማ ጎን ምንድን ነው? (ልታሻሽለው(ልታሻሽይው) ወይም ልታሳደገው(ልታሳድጊው) በሚገባህ(በሚገባሽ) ነገር ላይ ብቻ ትኩረትህን(ትኩረትሽን) አድርግ (አድርጊ)።

_____

_____

_____

_____

4. መሻሻልን በህይወትህ እና በአገልግሎትኸ ለማምጣት እኛ አብረን እየሰራን ሳለ፤አንተ ያንተን መሰጠት ሙሉ ለማድረግ (ለእያንዳንዱ ግብ) የምትወስዳቸው አንድ ፤ሁለት ብለኸ የምትገልጻቸው መሰረታዊ ተግባራዊ እርምጃዎች ምንድን ናቸው? (መሻሻልን የሚገዳደሩ ተግዳሮቶችን ለማስወገድ፡- በቅደም ተከተል መከተል የሚገባህን (የሚገባሽን) አስተማሪ (መካሪ) ነጥቦችን ጻፍ (ጻፊ)።

_____

_____ጊዜው_____

_____

_____ጊዜው_____

7. መንፈሳዊ ፍሬን እሻለሁ።

እኔ ፍሬ እንዳፈራ ተመርጫለሁ፡፡ ኢየሱስ መንፈሳዊ ፍሬ «በእርሱ ተደግፎ እና ጸንቶ በመቆም» እንደሚመጣ አስተምሯል፣ ምሳሌ ሆኖም አሳይቷል፡፡ እኔ መንፈሳዊ ውጤቶችን ወይም መንፈሳዊ ለውጦችን በሰዎች ሕይወት ውስጥ በራሴ ሰዋዊ ጥበብ እና በግል ጥረት በሚደረጉ ግፊቶች ማምጣት ወይም ማፍራት እንደማልችል ጠንቅቄ አውቃለሁ፡፡ የኔ ኃላፊነት ውጤቱን ለእግዚአብሔር ትቼ እራሴን በታማኝነት በስጦታዎቼ እና በጥሪዬ አማካኝነት ለሕዝቡ መስጠት ነው፡፡ የልቤ መሻት ኢየሱስን በመንፈሱ በመጓዝ እና በእርሱ ጸንቶ በመቆም ለክብሩ ብዙ ፍሬ ለማፍራት በእኔ እንዲሠራ በእርሱ አቅጣጫ መከተል ነው፡፡

(ማቴ. 7፡15-20፣ ማቴ. 16፡21-23፣ ዮሐ. 15፡1-11፣ 1ቆሮ. 1፡12፣ 1ጢሞ. 4፡6-16፣ 1ዮሐ. 2፡3-6)

1. እኔ አሁን በደረስኩበት የክርስትና ህይወትና አገልግሎት፡- ይኸ አንቀጽ ከሚያስተላልፈው መልህክት ውስጥ ለእኔ ጎላ ያለ ጠቀሜታ ያለው ነጥብ ምንድን ነው? (አንቀጹ ያዘለውን መልህክት ይዘህ(ይዘሽ) ለመቅረብ ሞክር(ሞክሪ)፡- አትቸኩል (አትቸኩዪ)።

_____

_____

_____

_____

2. በዚህ ጥናት መሠረት እራሴን ሳየው፡- ቀና የሆነ አስተዳደጌን ህይወቴ የሚያንጸባርቀው በምን መልኩ ነው? (አጽንዖት ስጥ(ስጪ) = የምታበረታታ ሁን(ሁኚ)

_____

_____

_____

_____

3. በዚህ አንቀጽ ከተንጸባረቀው መሰጠት ውስጥ አንድ ፤ሁለት ብዬ የምዘረዝረው የእኔ ደካማ ጎን ምንድን ነው? (ልታሻሽለው(ልታሻሽይው) ወይም ልታሳደገው(ልታሳድጊው) በሚገባህ(በሚገባሽ) ነገር ላይ ብቻ ትኩረትህን(ትኩረትሽን) አድርግ (አድርጊ)።

_____

_____

_____

_____

4. መሻሻልን በህይወትህ እና በአገልግሎትኸ ለማምጣት እኛ አብረን እየሰራን ሳለ፤አንተ ያንተን መሰጠት ሙሉ ለማድረግ (ለእያንዳንዱ ግብ) የምትወስዳቸው አንድ ፤ሁለት ብለኸ የምትገልጻቸው መሰረታዊ ተግባራዊ እርምጃዎች ምንድን ናቸው? (መሻሻልን የሚገዳደሩ ተግዳሮቶችን ለማስወገድ፡- በቅደም ተከተል መከተል የሚገባህን (የሚገባሽን) አስተማሪ (መካሪ) ነጥቦችን ጻፍ (ጻፊ)።

_____

_____ጊዜው_____

_____

_____ጊዜው_____

8. በትስስር እሠራለሁ።

እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ እና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እያንዳንዱ አካል የተለየ ኃላፊነት ያለው ሆኖ በፍጹም ኅብረት የሚንቀሳቀሱ አንድ ናቸው፡፡ ይህ የእነርሱ የተባበረ አመራር በየግል መገዛዛት አውድ ውስጥ የሚካሄድ ሲሆን ለእያንዳንዳቸው ሚና እና ተግባር ተገቢው ሥልጣን ያለበት ነው፡፡ እኔም በስላሴ ምሳሌነት እንደታየው የኅብረት አመራርን ለመሪዎች እንደ መስፈርት አድርጌ ተግባራዊ ላደርገው እሻለሁ፡፡ ከሌሎች አጋር መሪዎች ጋር በኅብረት እና በልዩ መቀባበል ለማገልገል እንድችል ጸጋ እንዲሰጠኝ እለምናለሁ፡፡

(ማቴ. 28፡16-20፤ ዮሐ. 5፡22-23፤ ዮሐ. 16. 13-15፤ ዮሐ. 17፡21፤ የሐዋ. 13፡1-3፤ ሮሜ 8፡14-17)

1. እኔ አሁን በደረስኩበት የክርስትና ህይወትና አገልግሎት፡- ይኸ አንቀጽ ከሚያስተላልፈው መልህክት ውስጥ ለእኔ ጎላ ያለ ጠቀሜታ ያለው ነጥብ ምንድን ነው? (አንቀጹ ያዘለውን መልህክት ይዘህ(ይዘሽ) ለመቅረብ ሞክር(ሞክሪ)፡- አትቸኩል (አትቸኩዪ)።

_____

_____

_____

_____

2. በዚህ ጥናት መሠረት እራሴን ሳየው፡- ቀና የሆነ አስተዳደጌን ህይወቴ የሚያንጸባርቀው በምን መልኩ ነው? (አጽንዖት ስጥ(ስጪ) = የምታበረታታ ሁን(ሁኚ)

_____

_____

_____

_____

3. በዚህ አንቀጽ ከተንጸባረቀው መሰጠት ውስጥ አንድ ፤ሁለት ብዬ የምዘረዝረው የእኔ ደካማ ጎን ምንድን ነው? (ልታሻሽለው(ልታሻሽይው) ወይም ልታሳደገው(ልታሳድጊው) በሚገባህ(በሚገባሽ) ነገር ላይ ብቻ ትኩረትህን(ትኩረትሽን) አድርግ (አድርጊ)።

_____

_____

_____

_____

4. መሻሻልን በህይወትህ እና በአገልግሎትኽ ለማምጣት እኛ አብረን እየሰራን ሳለ፤አንተ ያንተን መሰጠት ሙሉ ለማድረግ (ለእያንዳንዱ ግብ) የምትወስዳቸው አንድ ፤ሁለት ብለኽ የምትገልጻቸው መሰረታዊ ተግባራዊ እርምጃዎች ምንድን ናቸው? (መሻሻልን የሚገዳደሩ ተግዳሮቶችን ለማስወገድ፡- በቅደም ተከተል መከተል የሚገባህን (የሚገባሽን) አስተማሪ (መካሪ) ነጥቦችን ጻፍ (ጻፊ)።

_____

_____ጊዜው_____

_____

_____ጊዜው_____

9. ገንዘብን በታማኝነት እይዛለሁ።

ኢየሱስ እና ሐዋርያቱ ሁል ጊዜ የሌሎችን ገንዘብ ለአገልግሎት ዓላማ በታማኝነት ይይዙ ነበር፡፡ እነርሱ ባለአደራነትን በእግዚአብሔር እና በሕዝቡ ፊት ያለምንም ነቀፋ ፈጽመው በማሳየት አስተምረዋል እናም ምሳሌ ሆነዋል፡፡ አንዳንድ መሪዎች በሰዎች ገንዘብ ያለ አግባብ ሲጠቀሙ ወይም ለአገልግሎት ሌሎች መንፈሳዊ መሪዎች በሰጡት ገንዘብ ላይ ታማኝነት ማግኘት ሲያቅታቸው ስመለከት አዝናለሁ፡፡ እኔ የገንዘብ ፍቅር የመሪዎችን የኢየሱስን መንግስት ለማገልገል ያላቸውን ብቃት እንደሚያዛባ እና የመንፈሳዊነት ፈተናን እንዲወድቁ እንደሚያደርግ አውቃለሁ፡፡ እንዲሁም መሪዎች ቤተሰባቸውን ሊደግፉ እንደሚገባ እና ከሚያገለግሏቸው ሕዝብ የኑሮ ድጋፍ ማግኘትን እንደመብት ሊጠብቁ እንደሚገባም እውቅና ሰጣለሁ፡፡ እኔ በእግዚአብሔር እና በሕዝቡ ፊት እኔ ታምኜ በተሾምኩበት ገንዘብ ላይ ያለ ምንምነቀፋ ማገልገል እና መንቀሳቀስ እንድችል በትህትና እለምናለሁ/ እጸልያለሁ፡፡

(ማቴ. 6፡25-34፣ ሉቃ. 16፡14-15፣ ሐዋ. 4፡32፤ 5-11፣ ሐዋ. 20፡25-35፣ 1ቆሮ. 9፡1-18፡ 2ቆሮ. 8፡16-22፣ 1ጢሞ. 6፡9- 11፣ 1ጴጥ. 5፡2-3፣ ይሁዳ 11-12)

1. እኔ አሁን በደረስኩበት የክርስትና ህይወትና አገልግሎት፡- ይኸ አንቀጽ ከሚያስተላልፈው መልህክት ውስጥ ለእኔ ጎላ ያለ ጠቀሜታ ያለው ነጥብ ምንድን ነው? (አንቀጹ ያዘለውን መልህክት ይዘህ(ይዘሽ) ለመቅረብ ሞክር(ሞክሪ)፡- አትቸኩል (አትቸኩዪ)።

_____

_____

_____

_____

2. በዚህ ጥናት መሠረት እራሴን ሳየው፡- ቀና የሆነ አስተዳደጌን ህይወቴ የሚያንጸባርቀው በምን መልኩ ነው? (አጽንዖት ስጥ(ስጪ) = የምታበረታታ ሁን(ሁኚ)

_____

_____

_____

_____

3. በዚህ አንቀጽ ከተንጸባረቀው መሰጠት ውስጥ አንድ ፤ሁለት ብዬ የምዘረዝረው የእኔ ደካማ ጎን ምንድን ነው? (ልታሻሽለው(ልታሻሽይው) ወይም ልታሳደገው(ልታሳድጊው) በሚገባህ(በሚገባሽ) ነገር ላይ ብቻ ትኩረትህን(ትኩረትሽን) አድርግ (አድርጊ)።

_____

_____

_____

_____

4. መሻሻልን በህይወትህ እና በአገልግሎትኽ ለማምጣት እኛ አብረን እየሰራን ሳለ፤አንተ ያንተን መሰጠት ሙሉ ለማድረግ (ለእያንዳንዱ ግብ) የምትወስዳቸው አንድ ፤ሁለት ብለኽ የምትገልጻቸው መሰረታዊ ተግባራዊ እርምጃዎች ምንድን ናቸው? (መሻሻልን የሚገዳደሩ ተግዳሮቶችን ለማስወገድ፡- በቅደም ተከተል መከተል የሚገባህን (የሚገባሽን) አስተማሪ (መካሪ) ነጥቦችን ጻፍ (ጻፊ)።

_____

_____ጊዜው_____

_____

_____ጊዜው_____

10. ለማገልገል ልዩ ልዩ ማዕቀፎችን እጠቀማለሁ።

ልዩ ልዩ ስልቶች እና ተቋማት (ማዕቀፎች) ለቤተ ክርስቲያናት እና አገልግሎቶች የባለአደራነት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡ በኢየሱስ ዘመን ፈሪሳውያን እና ጻፎች ኢየሱስን የራሳቸውን ልዩ ልዩ የባህላዊ ማዕቀፎች ተቋም ህጎች ማስረጃዎች እና ስነ መለኮትን በተቃራኒው በመጠቀም ሲቃወሙት እንደነበር ሳይ እደነቃለሁ፡፡ በዚህ ዘመን በርካታ መሪዎች በተመሳሳይ መልኩ የሰዎችን መሰጠት ከክርስቶስ ይልቅ ወደ ራሳቸው፣ ወደ አሠራራቸው፣ ወደ ቁሳቁሶቻቸው ወይም ስነ መለኮዊ መርሃቸው ሲያዞሩ እና ለመቆጣጠር ሲፈተኑ ሳይ አዝናለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜ መሪዎች የራሳቸው ተቆጣጣሪነት እና ተጽእኖ ለማጽናት ኃላፊነት የእነርሱ ብቻ ሲያደርጉ እና ልዩ ልዩ ተዋረዶችን ደረጃዎችን ሲፈጥሩ እና ማዕረጎችን ሲያበጁ እመለከታለሁ፡፡ «ጌታ መሆን» እና እቅድ፣ ራእይ እና መዋቅራዊ ግዴታን በመጫን ሰዎችን መጉዳት ቀላል ነው፡፡ አኔ እራሴን ላነጻ እና ንጉሴን በቅድስናና እና በመልካም ላገለግል እንዲሁም የማገለግላቸውን ሌሎችን ከእርሱ ጋር የቀረበ ግንኙነት (እርምጃ) እንዲኖራቸው ለማገዝ እጠማለሁ፡፡

(ማቴ. 23፡13-33፤ ዮሐ. 11፡47-48፣53፤ የሐዋ. 20፡18-35፤ ፊሊ. 2፡19-21፤ ያዕቆብ 4፡13-16፤ 1ኛጴጥ. 5፡2-3፤ 3ኛዮሐ. 9-11)

1. እኔ አሁን በደረስኩበት የክርስትና ህይወትና አገልግሎት፡- ይኸ አንቀጽ ከሚያስተላልፈው መልህክት ውስጥ ለእኔ ጎላ ያለ ጠቀሜታ ያለው ነጥብ ምንድን ነው? (አንቀጹ ያዘለውን መልህክት ይዘህ(ይዘሽ) ለመቅረብ ሞክር(ሞክሪ)፡- አትቸኩል (አትቸኩዪ)።

_____

_____

_____

_____

2. በዚህ ጥናት መሠረት እራሴን ሳየው፡- ቀና የሆነ አስተዳደጌን ህይወቴ የሚያንጸባርቀው በምን መልኩ ነው? (አጽንዖት ስጥ(ስጪ) = የምታበረታታ ሁን(ሁኚ)

_____

_____

_____

_____

3. በዚህ አንቀጽ ከተንጸባረቀው መሰጠት ውስጥ አንድ ፤ሁለት ብዬ የምዘረዝረው የእኔ ደካማ ጎን ምንድን ነው? (ልታሻሽለው(ልታሻሽይው) ወይም ልታሳደገው(ልታሳድጊው) በሚገባህ(በሚገባሽ) ነገር ላይ ብቻ ትኩረትህን(ትኩረትሽን) አድርግ (አድርጊ)።

_____

_____

_____

_____

4. መሻሻልን በህይወትህ እና በአገልግሎትኽ ለማምጣት እኛ አብረን እየሰራን ሳለ፤አንተ ያንተን መሰጠት ሙሉ ለማድረግ (ለእያንዳንዱ ግብ) የምትወስዳቸው አንድ ፤ሁለት ብለኽ የምትገልጻቸው መሰረታዊ ተግባራዊ እርምጃዎች ምንድን ናቸው? (መሻሻልን የሚገዳደሩ ተግዳሮቶችን ለማስወገድ፡- በቅደም ተከተል መከተል የሚገባህን (የሚገባሽን) አስተማሪ (መካሪ) ነጥቦችን ጻፍ (ጻፊ)።

_____

_____ጊዜው_____

_____

_____ጊዜው_____

ቃለ ኪዳን በግል

ከእኔ በፊት የነበሩ መሪዎች በመሠረቱት መሠረት ላይ እየገነባው ቆሚያለሁ።እነርሱ ፍጹም አልነበሩም፤ እኔም ፍጹም አይደለሁም። በተማሩት መሰረት፣ በጌታ ጸጋና መልካምነት፤ እንዲሁም በእነርሱ ሆኖ መንግስቱን በሚያሰፋው በእርሱ ሆነው ህዝቡን መሩ።

በጌታዬ በኢየሱስ ፊት ሆኜ እንደመሪ ድካሜን እናዘዛለሁ።

ኢየሱስን እንድመስልና ሌሎችንም እንዲሁ ለማጎልበት እንድችል በአብ፤ በወልድ፤ በመንፈስቅዱስ ስም እራሴን በትህትና እሰጣለሁ። እግዚአብሔር በጸጋውና በምህረቱ ለዚህ ቃል ኪዳን ታማኝ እንድሆን ይርዳኝ። አሜን።

በዓለም ሁሉ የሚገኙትን መሪዎች በመቀላቀል ይህንን የግል ቃልኪዳኔ አደርጊያለሁ።

ፊርማ _____

ቀን _____

ምስክር _____

ምስክር _____